# የዐርዝ ቻርተር (የምድር መተዳደርያ ደንብ)

**መቅድም**

ሁላችንም  በምድር ታሪክ ዉስጥ የሰው ልጅ የወደፊት እጣ ፈንታዉን በሚወስንበት ወሳኝ ሰአት ላይ እንገኛለን፡፡ የአለማችን  ሀገሮች በከፍተኛ ሁኔታ እርስ በርስ በተገናኙበት ዘመን መጭዉ ግዜ ተስፋንም አደገኛ ሁኔታንም ያዘለ ይሆናል፡፡

ወደፊት ለመራመድ ፤ ምንም እንኳ አለማችን የባህል ልዩነት እና ብዝሀ ህይወት የሞሉባት ብትሆንም፤ ሁላችንም የጋራ እጣ ፈንታ ያለን የአንድ ፍጥረት ቤተሰብ፣ የአንድ ምድር ማህበረሰብ መሆናችንን መገንዘብ አለብን፡፡ ስለዚህም ሁላችንም ተፈጥሮን በማክበር፣ አለም አቀፋዊ ሰብአዊ መብት፣ የሰላም ባህል እና ኢኮኖሚያዊ ፍትህ ላይ የተመሰረተ ዘላቂነት ያለው የአለም ሕብረተሰብ ለማምጣት እጅ ለእጅ መያያዝ አለብን፡፡ በስተመጨረሻም እኛ የምድር ህዝቦች ለተሻለ ህይወትና  ለመጭው ትውልድ ሲባል እርስ በእርስ ለመደጋገፍ ያለብንን ሀላፊነት መግለፅ ይገባናል፡፡

**ምድር-መኖርያችን**

የሰው ፍጥረት የሁሉም ፍጥረታት አካል ነው፡፡ ስለዚህም ምድር የሰው ልጆች መኖርያ ብትሆንም ሌሎች ፍጥረታትን አዝላ ህያው የሆነች ናት፡፡ የተፈጥሮ ግፊት የህይወት ቆይታን አስቸጋሪ እና የማይታመን ቢያደርገውም፤ ነገር ግን ምድር ህይወት ቀስ በቀስ እንዲዳብር አስፈላጊውን ሁኔታ ታመቻቻለች፡፡ የህይወት ስብስብ ቶሎ የማገገም ፀባይ እና የሰው ልጅ ደህንነት፤ የበዛ ልዩነት ያላቸው እንስሰሳትና አፅዋት መኖርና ፣ የለማ መሬት፣ ንጹህ አየር እና ዉሀን ያካተተ ጤናማ የሆነ ብዝሀ ሕይወት ከነሙሉ ኢኮሎጂያዊ ቀመር ጠብቆ በማቆየት ላይ ይወሰናል፡፡ በአለማችን ላይ ዉስን የሆነ ሀብት መኖሩ ለሁሉም ማህበረሰብ አሳሳቢ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህም የምድርን ሕያውነት፣ ልዩነትና ዉበት ጠብቆ ማቆየት የተቀደሰ ሀሳብ ነው፡፡

**የአለማችን ሁኔታ**

በአለማችን በብዛት የሚታየው የአመራረትና የተመረተውን የመጠቀም ሂደት የተፈጥሮ ሀብትን የሚያውድም ፣ ብዝሀ ሕይወትን የሚያመነምን በአጠቃላይ የተፈጥሮ አከባቢን የሚጎዳ ነው፡፡ አከባቢዎች እየተጎዱ ነው፡፡ የእድገት ጥቅም እኩል ለሁሉም ህብረተሰብ አይደርስም፤ ስለዚህም የሃብታንና ድሀ ልዩነት እየበዛ ነው፡፡ ኢፍትሃዊነት፣ ድህነት፣ አለማወቅ እና ጦርነት እየተስፋፉና ስቃይን እያስከተሉ ነዉ፡፡ በአለማችን ሳይጠበቅ የተንሰራፋዉ የሰው ህዝብ ብዛት የኢኮሎጂንና የማህበረሰብን ቀመር እያጨናነቀ ይገኛል፡፡ የአለም ዋስትና መሰረቶች በስጋት ዉስጥ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች አደገኛ ቢሆኑም የማይቀሩ ክስተቶች ናቸው፡፡

**የወደፊት አዳጋች ሁኔታዎች**

የሰው ልጅ ሁለት ምርጫ አለው፡፡ አለም አቀፋዊ ትብብርን መስርቶ እርስ በእርስ መደጋገፍ እና መሬትን መንከባከብ አለበለዚያም በሰው ልጅ እንዲሁም በብዝሀ ህይወት ላይ ሊደርሱ የሚችሉትን አደጋዎች

መቀበል፡፡ ስር ነቀል ለውጦች፤ የሰው ልጅን አመለካከት ፣ አሰራሮችንና አኗኗርን አስመልክቶ ያስፈልጋሉ፡፡ መረዳት ያለብን ነገር የሰው ልጆች መሰረታዊ ፍላጎቶች ሲሟሉ ፤ የሰው እድገት የሚገለጸው ብዙ በማግኘት ሳይሆን በሁሉ መልኩ የጎለበተ ህይወት በመያዝ ነው፡፡ እኛ የሰው ልጆች ሁሉንም ለመመገብ የሚያስችልና ሰው ሰራሽ የሆነ አደጋን ለመቀነስ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች አሉን፡፡ የሲቪል ማህበረሰብ በአለማችን ላይ ማበብ ዲሞክራሲና ሰብአዊ አለም ለመገንባት አዳዲስ እድሎችን በመፍጠር ላይ ይገኛል፡፡ የተፈጥሮ አከባቢችን፣ ኢኮኖሚያችን፣ ፖለቲካችን፣ ማህበራዊ እና መንፈሳዊ አዳጋች ሁኔታዎች እርስ በእርስ የተገናኙ ናቸው፡፡ እጅ ለእጅ በመያያዝ ሁሉን አዘል መፍትሄ መፍጠር ይቻላል፡፡

**አለም አቀፍ ግዴታዎች**

ከላይ የተዘረዘሩትን እቅዶች እውን ለማድረግ አለም አቀፋዊ የሀላፊነት አመለካከት መኖርና ራሳችንን እንደ አንድ የጠቅላላው የምድር ማህበረሰብ አካል እንዲሁም የአቅራቢያችን መንደር አካል ለመመልከት መወሰን አለብን፡፡ እኛ የተለያዩ አገሮች እንዲሁም የአንድ አለም ዜጎች ነን፡፡ ይህም የሚያመለክተዉ የአቅራቢያችን ሁኔታ እና አለም አቀፋዊ ሁኔታዎች እርስ በእርስ የተቆላለፉ መሆናቸውን ነው፡፡ ሁሉም ሰው የዛሬውንና የነገውን የሰው ልጆችንና የጠቅላላው አለም የህይወት አካላትን ደህንነት ለመጠበቅ ሀላፊነት አለበት፡፡ የሰው ልጆች ህብረትና የሰው ልጆች ከሌላው የህይወት አካላት ጋር ያለቸው የዝምድና መንፈስ የሚጎለብተው በተፈጥሮ የተሰጠንን ጸጋ አመስግነን ስንኖርና፣ የመኖርን ሚስጢር በመገንዘብና የሰው ልጅ በተፈጥሮ የያዘውን ቦታ በክብር ስንይዝ ነው፡፡

ለመጭው የአለም ማህበረሰብ በስነምግባር የታነፀ የኑሮ መሰረት ለመጣል በተፋጠነ መልኩ የጋራ እሴቶችና መሰረታዊ ዋጋዎች ሊኖሩን ይገባል፡፡፡ ሰለዚህም ሁላችንም አንድ ላይ በመሆን ዘላቂ የሆነ አኗኗር ለማምጣት ለመሰረታዊ ስነስርአት ሁሉም የሰው ልጆች ፣ ድርጅቶች፣ ቢዝነሶች፣ መንግስታት፣ ወቅታዊ ተቅዋማት ሊመሩባትና ሊመዝኑባት ሊሆኑ የሚችሉ፤ የሚከተሉትን ተያያዥነት ያላቸውን መሰረታዊ ሀሳቦች በጋራ ሁነን እናረጋግጣለን፡፡

***ሀ. ክብርና እንክብካቤ ለፍጥረታት ማህበረሰብ***

***መርሆዎች***

1. ምድርንና ብዝሃ ህይወቶችን ማክበር፡፡

   ሀ) ሁሉም ፍጥረታት እርስ በርስ የተያያዙ እንደሆኑና ማንኛውም የፍጥረት አካል ለሰው ልጅ ጠቃሚ ይሁንም አይሁንም ዋጋ እንዳለው መረዳት፡፡

   ለ) በሠው ልጅ መሰረታዊ ክብር እና በፍጥረታት አእምሮአዊ፣ አርቲስቲካዊ፣ ስነምግባራዊ እና መንፈሳዊ ችሎታዎች ላይ እምነት ማኖር ፡፡

2. የፍጥረታት ማሕበረሰብ በፍቅር፣ በርህራሄ እና በማስተዋል መንከባከብ፡፡

ሀ) የተፈጥሮ ሀብትን ባለቤት በመሆን፣ በመቆጣጠር እንዲሁም ከመጠቀም ጋር ተያይዞ የአከባቢን ጉዳት የመቀነስና የሠው ልጆች መብትን የመጠበቅ ሃለፊነት እነደአለ አምኖ መቀበል፡፡

ለ) ከላቀ ነፃነት፣ዕውቀት እና ሀይል ጋር ተያይዞ የጋራ ጥቅምን የማስከበር የላቀ ሀላፊነት እንደአለ ማረጋገጥ፡፡

3. ፍትሃዊ፣ አሣታፊ፣ ዘላቂ እና ሠላማዊ የሆኑ የዲሞክራሲ ማህበረሰቦችን መገንባት፡፡

ሀ) በማንኛውም ደረጃ ላይ ያሉ ማህበረሰባት ሰብአዊ መብታቸው እና መሰረታዊ ነፃነታቸውን እንዲያረጋግጡና እያንዳንዱ ሰው ሙሉ ችሎታውን የመጠቀም እድል እንዲኖረው ማደርግ፡፡

ለ) ኢኮሎጂካዊ ሀላፊነትን ያገናዘበ ጥሩ አኗኗር ለማግኘትና ለመረጋገጥ የሚያስችሉ ማህበረሰባዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፍትሆዎችን ማበረታት

4. የምድርን ቁኝጅናና ለጋሽነት ለአሁንም ለወደፊትም ትውልድ ማፅናት፡፡

ሀ) የእያንዳንዱ ትውልድ እንቅስቃሴ በመጪው ትውልድ ፍላጎት እንደሚወሰን መገንዘብ ፡፡

ለ) በዘላቂ መልኩ በምድር ላይ የሚኖሩ የሰው ልጆችንና እና ኢኮሎጂካዊ ማሕበረሰቦችን የሚደግፉ እሴቶችን፣ ባህሎችንና ተቅዋማትን ለወደፊት ትውልድ ማስተላለፍ፡፡

እነዚህን አራት ትልልቅ ግዴታዎች ለሟሟላት ከታች የሚዘረዘሩት ወሳኝ ናቸው፡፡

**ለ) ኢኮሎጂያዊ ሙሉዕነት**

*መርሆዎች*

5. ለባይሎጂካል ስብጥርነትና ህይወትን ለማቆየት ለሚረዱ የተፈጥሮ ሂደቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት የምድርን ኢኮሎጂካዊ ቀመሮች ሙሉዕነት መጠበቅ እና ማቆየት፡፡

ሀ) በየትኛውም ደረጃ ዘለቄታዊነት ያላቸውን የልማት ፕላኖችና የአከባቢ ጥበቃንና ማገገሚያን ያመከሉ የልማት ተነሣሽነቶችን ማፅደቅ፡፡

ለ) የምድር ህይወትን ደጋፊ ቀመሮችን ለመጠበቅ፣ ብዝሀ ህይወትን ለማቆየት ፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን ለማቆየት፤ የተፈጥሮንና እና የብዝሃ ህይወት ክምችቶችን መጠበቅና መንከባከብ አለብን፡፡

ሐ) በአደጋ ላይ ያሉ ህይወታትን እና ኢኮሲስተሞችን መንሠራራት ማበረታታት፡፡

መ) በተፈጥሮ ላሉ ዝርያዎችና እና ለአከባቢ ጠንቅ የሆኑ በተፈጥሮ ያልተገኙ ወይም ጀነቲካሊ በአርተፊሻል መልኩ የተስተካከሉ ፍጥረቶችን ማጥፋትና መቆጣጠር እንዲሁም እነዚህን የመሳሰሉ አደገኛ ነፍሳትን ለወደፊት እንዳይፈጠሩ መከላከል፡፡

ሠ) ሊተኩና ሊታደሱ የሚችሉ እንደውሃ፣ አፈር የጫካ ምርቶችንና የውቅያኖስ ህይወታትን የመሰሉ ሀብቶችን አጠቃቀም የመራባት መጠን ባለለፈ መልኩ እና የኢኮሲስተም ጤንነት በጠበቀ መልኩ በሚገባ ማስተዳደር፡፡

ረ) ሊተኩና ሊታደሱ የማይችሉ እንደማዕድን፣ የፎሲል ነዳጅ የመሳሰሉትን ሀብቶች፤ መመናመንና የአከባቢ ጠንቅ በማያስከትል መልኩ ማስተዳደር፡፡

6. አስቀድሞ የሚመጣ አደጋን መከላከል እንደጥሩ የአከባቢ ጥበቃ ዘዴ መጠቀም፤ በተለይም በዘርፉ ያለው እውቀት አነስተኛ ሲሆን፤ አስቀድሞ ከሚኖሩ ችግሮች መጠንቀቅን እንደ መፍትሄ መውሰድ፡፡

ሀ) ሣይንሳዊ እውቀት ያልተሟላ የሚሆንበትን ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ አስገብቶ ሊስተካከሉ የማይችሉ የተፈጥሮ አከባቢን ሊጎዱ የሚችሉ ተግባራትን ማስወገድ፡፡

ለ) በተግባር ሊውሉ የታቀዱ ስራዎቻቸው ምንም አይነት የአከባቢ ጉዳት አያስከትልም በሚሉ አካሎች ላይ ይህንን ክስተት ሊፈጥር እንደማይችል የሚያስረዳ ጠበቅ ያለ ማስረጃ መጠየቅ፤ እነዚህንም አካሎች ሊፈጠር በሚችለው የአከባቢ ጉዳት ሃላፊነት እንዲወስዱ ማድረግ፡፡

ሐ) ዉሳኔዎች የወደፊቱን፣ የሩቁን፣ በተዘዋዋሪ ሊደርሱ የሚችሉ በሰው ልጆች የሚፈጠሩ የአለም ላይ ክስተቶችን ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡

መ) ማንኛውንም አይነት የአከባቢ ብክለት መከላከል፡፡ እንዲሁም መርዛማ፣ ሬድዮ አክቲቭ እና እነዚህን የመሳሰሉ አደገኛ ንጥረ ነገሮች እንዳይመረቱ ማድረግ፡፡

ሠ) አከባቢን የሚጎዱ ወታደራዊ ድርጊቶችን ማስወገድ፡፡

7. የምድርን የማምረት ብቃት እና የሰው ልጆችን እና የአከባቢን ደህንነት የሚጠብቁ የአመራረት፣ የአመጋገብና እና የመራባት ሂደቶችን መተግበር፡፡

ሀ) በአመራረት እና በአመጋገብ ሂደት ላይ የምንጠቀምባቸውን ግብአቶች መቀነስ፡፡ እንዲሁም በድጋሚ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ እነዚህም እቃዎች የሚፈጥሩት ዝቃጅ በኢኮሎጂካል መዋቅር ተቀባይነት እንዲኖረው ማድረግ፡፡

ለ) ሀይልን በብቃት እና በቁጠባ መጠቀም፡፡ እንዲሁም ሊታደሱ የሚችሉ እንደ ፀሀይ፣ ውሃና ንፋስ ያሉ የሀይል ምንጮችን አብዝቶ መጠቀም፡፡

ሐ) አከባቢን የሚጠብቁ ቴክኖሎጂዎችን መገንባት፣ መጠቀም እንዲሁም እኩል በሆነ መልኩ ለሁሉም መስተላለፍን መበረታታት፡፡

መ) በእቃዎች መሸጫ ዋጋዎች ላይ የአከባቢያዊ እና የማህበራዊ ወጪዎችን ማካተት፡፡ እንዲሁም ተጠቃሚዎች የላቀ የአከባቢ እና የማህበራዊ መመዘኛዎችን ያሟሉ እቃዎችን ለይተው እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

ሠ) የስነተዋልዶ ጤንነትና እና ሃላፊነትን ያገናዘበ ስነተዋልዶን የሚያበረታታ አለምአቀፋዊ የጤና አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ፡፡

ረ) አለም የተወሰነ ሀብት እንዳላትና ተያይዞም የቁሳቁስ ምጠና እንደሚያስፈልግና ከቁሳቁስ ብዛት እና ከሚቆጠር ሀብት የበለጠ ደስታ የተሞላበት ህይወት ለመኖር ትኩረት የሚሰጡ የአኗኗር ዘይቤዎችን መተግበር፡፡

8. የኢኮሎጂን ዘላቂነት ላይ ያተኮሩ ጥናቶችን ማጠናከር፡፡ እንዲሁም የተገኙ እውቀቶችንና በነፃ መለዋወጥና በብዛት ጥቅም ላይ እንዲውል ማደረግ፡፡

ሀ) በማደግ ላይ ያሉ አገሮችን ፍላጎት በበለጠ ግምት ውስጥ ያስገባ ዘላቂያዊነትን አስመልክቶ አለም አቀፋዊ የሳይንስ እና የቴክኖሎጂ ትብብሮችን ማድረግ፡፡

ለ) ለአከባቢ ጥበቃና ለሰው ልጅ ደህንነትን አስተዋፅኦ የሚያደርጉ በየትኛውም ባህል የሚገኙ የባህል እውቀቶችንና የመንፈሳዊ ጥበቦችን መጠበቅ እንዲሁም እውቅናን መስጠት፡፡

ሐ) ለሰው ልጅ ጤንነትና ለአከባቢ ጥበቃ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ጀነቲክ መረጃዎችን ጨምሮ ለአብዛኛው ማህበረሰብ በቀላሉ እንዲገኝ ማደረግ፡፡

# ሐ) ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍትህ

***መርሆዎች***

9. ድህነት ስነምግባርን ማህበረሰብ እና አከባቢን አስመልክቶ ተኩረት እንደሚሻ ተገንዝቦ ማጥፋት

ሀ) አስፈላጊውን የሀገር ውስጥና የአለም አቀፍ ሀብቶችን ተጠቅሞ የንፁህ ውሃ፣ ንፁህ አየር፣ የምግብ ዋስትና፣ ያልተበከለ አፈር፣ መጠለያ እንዲሁም ጉዳት የማያስከትል መፀዳጃ የማግኘት መብትን ማረጋገጥ፡፡

ለ) ማንኛውም/ዋም የሠው ልጅ ዘላቂ የሆነ ኑሮ እንዲኖር/እንድትኖር የሚያስቸልውን/ችላትን ትምህርት እና ሃብት እንዲኖረው/ራት ማድረግ፡፡ እንዲሁም ራሳቸውን መደገፍ ለማይችሉት ደግሞ ሴፍቲኔት እና የማህበራዊ ዋስትና መስጠት፡፡

ሐ) የተረሱትን የሰው ልጆች እናስታውስ፣ ለችግር የተጋለጡትን እንጠብቅ፣ የሚሰቃዩትን እንርዳ፤ እንዲሁም ሁሉም ችሎታቸውን እንዲያዳብሩና ምኞታቸውን እንዲያሳኩ እናድርጋቸው፡፡

10. በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችና ተቅዋማት በእኩልነትና በዘላቂነት ላይ የተመሰረተ የሰው ልጅ ሁለንተናዊ እድገትን የሚያበራቱ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡

ሀ) በሁሉም አገራት ውስጥ እና መካከል ሚዛናዊ የሆኑ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር ማበረታታት፡፡

ለ) በማደግ ላይ ያሉ አገሮችን አእምሮአዊ፣ ገንዘባዊ፣ ቴክኒካዊና ማህበራዊ ሀብቶችን ማሻሻል፡፡ እንዲሁም እነዚህን ሀገሮች ከከባድ አለም አቀፋዊ የገንዘብ ብድር ነፃ ማውጣት፡፡

ሐ) ሁሉም የንግድ አይነቶች ዘላቂያዊ የሆነ የሀብት አጠቃቀም፣ የአከባቢ ጥበቃንና እና የተሻሻሉ የሰው ሐይል መመዘኛዎችን የሚደግፉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፡፡

መ) ብዝኃሀገራዊ ኮርፖሬሽኖችና አለም አቀፋዊ የገንዘብ ተቅዋማት ለህዝብ ጥቅም በኃላፊነት እንዲያገለግሉ ማድረግ እንዲሁም እነዚህ ተቅዋማት ስራዎቻቸው ለሚያስከትሉአቸው መዘዝዎች ተጠያቂ ማድረግ፡፡

11. የፆታ እኩልነት ለዘላቂያዊ ልማት መሟሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ መሆኑን ማረጋገጥ፤ እንዲሁም አለምአቀፋዊ የትምህርት፣ የጤና ጥበቃ እና የኢኮኖሚ እድሎች እንዲኖሩ ማድረግ፡፡

ሀ) የልጃገረዶችንና የሴቶችን ሰብአዊ መብቶችን ማረጋገጥ፤ የሚደርስባቸውንም ሁሉንም አይነት ጥቃቶች ማብቃት፡፡

ለ) የሴቶችን እኩል አጋርነት፣ ውሳኔ ሰጪነት፣ መሪነት እና ተጠቃሚነት አስመልክቶ በሁሉም ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ሲቪላዊ ዘርፎች የሴቶችን ንቁ ተሳትፎ ማበረታታት፡፡

12. ያለምንም ተፈጥሮአዊና፣ ማህበረሰባዊ መድልኦ የሰውን ልጅ ክብር፣የሰውነት ጤና፣ የመንፈስ ሕይወት ሁኔታዎችን የሚደግፉ እንዲሁም ለአናሳ ማህበረሰቦች የተለየ ትኩረት በመስጠት ያለምንም መድልኦ የሁሉንም ሰው ክብር ማስከበር፡፡

ሀ) ሁሉንም አይነት መድልኦዎች ማጥፋት፡፡ እንደ ዘር፣ ቀለም፣ ፆታ፣ ፆታዊ አመለካከት፣ ሀይማኖት፣ ቋንቋ እና በአገር፣ በዘር፣ በማህበራዊ አመጣጥ ተመርኩዘው የሚደረጉ መድልኦዎችን ማጥፋት፡፡

ለ) የኢንዲጂንየስ(የጥንታዊ) ህዝቦችን መንፈሳዊነት፣ እውቀት፣ መሬት፣ ሀብት እና ለዘላቂ ኑሮ የሚከተሉአቸውን ዘዴዎች ተያይዞ ያሉትን መብቶችን ማረጋገጥ፡፡

ሐ) ወጣቶችን ማክበርና ማበረታታት፤ እንዲሁም ለዘላቂያዊ ማህበረሰብን መገንባት የድርሻቸውን እንዲያበረክቱ ማድረግ፡፡

መ) ለባህልና ለመንፈስ ጠቃሚነት ያላቸውን ስፍራዎች መጠበቅና እንዲሁም ወደነበሩበት ይዞታ እንዲመለሱ ማድረግ፡፡

# (መ) ዲሞክራሲ፣ የብጥብጥ አለመኖርና ሰላም

***መርሆዎች***

13. በየትኛውም ደረጃ ያሚገኙ ዲሞክራሲያዊ ተቅዋማትን ማጠናከር እንዲሁም በአስተዳደር ውስጥ ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲኖርና ሁሉን ያሳተፈ ውሳኔ ሰጪነት እና ፍትህን የማግኘት እድል እንዲኖር ማድረግ፡፡

ሀ) ማንኛውም ሰው የተፈጥሮ አከባቢንና የሚመለከቱትን(ታትን) ወይንም ፍላጎት ያሰዳረበትን(ባትን) ሁሉንም የልማት እቅዶችንና እንቅስቃሴዎችን አስመልክቶ የተጣራ እና ጊዜያዊ የሆነ መረጃ የማግኘት መብት እንዲኖረው(ራት) ማድረግ፡፡

ለ) አከባቢያዊ፣ ክልላዊ እና አለምአቀፋዊ የሲቪል ማህበረሰቦችን መደገፍ፡፡ እንዲሁም ሁሉንም በጉዳዩ ላይ ፍላጎት ያላቸውን ሰዎችና እና ድርጅቶች በውሳኔ አሰጠጥ ላይ በደንብ እንዲሳተፉ ማድረግ፡፡

ሐ) ሃሳብን በነፃ የመግለፅን፣ ሰላማዊ የሆኑ ስብሰባዎችን የማድረግ ፣ ማህበሮችና የማቋቋም እና ሰላማዊ ተቃውሞዎችን የማድረግ መብቶችን መጠበቅ፡፡

መ) የተፍጥሮ አከባቢ ጉዳቶችን እንዲሁም የወደፊት ይህን መሰል አደጋዎችን ለመቀንስ መፍትሄዎችን ያካታተቱ ብቁና ወጪን ያገናዘቡ ፍትህን የማግኘት መሰረቶችን ማደራጀት፡፡

ሠ) ሙስናን በሁሉም የመንግስትም ሆኑ የግል ተቅዋማት ውስጥ ማጥፋት፡፡

ረ) በአቅራቢያ ያሉ ህብረተሰቦችን ማጠናከር እንዲሁም የተፈጥሮ አከባቢያቸውን እንዲንከባከቡ ማስቻል፤ የተፈጥሮ አከባቢ አስመልክቶ እስከመንግስት ደረጃ( በደንብ ጉዳዮች እንዲፈፀሙ ስለሚረዳ) ሊያደርሱ የሚችሉ ሀላፊነቶችንም መስጠት፡፡

14. በመደበኛ ትምህርትና በህይወት ዘመን ሁሉ በሚኖር እውቀት ውስጥ ዘላቂ ህይወት ለመምራት የሚያስችሉ እሴቶችንና ክህሎቶችን ማካተት፡፡

ሀ) ለዘላቂ ልማት አስተዋፅኦ ለማድረግ የሚያስችሉ ትምህሮችን ሁሉም የህብረተሰብ አካላት በተለይም ህፃናትና ወጣቶች እንዲቀስሙ ማድረግ፡፡

ለ) የጥበብን፣ የሰዋሰው እውቀትንና ሳይንስ ለዘላቂ ትምህርት የሚያደርጉትን አስተዋፅኦ ማበረታት፡፡

ሐ) ማስሚድያ ኢኮሎጂካል እና ማህበራዊ ጫናዎችን አስመልክቶ እውቀትን በማስጨበጥ ረገድ የሚያድረገውን ሚና ማጎልበት፡፡

መ) የሞራልና የመንፈሳዊ ትምህርቶች ለዘላቂ አኗኗር የሚኖራቸውን አስፈላጊነት መገንዘብ፡፡

15. ሁሉንም የህይወት አካላት በክብርና በመረዳት መንከባከብ፡፡

ሀ) በሰው ልጅ መሀከል እንስሳትን አስመልክቶ ያለን ጭካኔ መከላከል እንዲሁም እንስሳትን ከስቃይ መታደግ፡፡

ለ)የዱር እንስሳትን ከአደን ከአፈናና በጣም አደገኛና ለረጅም ግዜ የሚቆይ ስቀይን ሊያስከትሉ ከሚችሉ ማጥመድ መከላከል፡፡

ሐ) በአላማ ውስጥ ያልተካተቱ ዝርያዎችን ከመጉዳት ወይም ህይወት ከማጉደል ሙሉ በሙሉ መቆጠብ፡፡

16. የመቻቻል፣ የብጥብጥ አልባነትና የሰላምን ባህል ማዳበር፡፡

ሀ) በሰዎች መካከል እና በአገራት መካከል የሚገኝን የጋራ መግባባትን፣ ህብረትን እና ትብብርን ማበረታት እንዲሁም መደገፍ

ለ) ረብሻና ግጭትን ለመከላከል የሚያስችሉ ሁለንትናዊ የሆኑ ስትራተጂዎችን መተግበር፡፡ እንዲሁም በትብብር ላይ የተመሰረተ ችግርን የመፍቻ ዘዴን የተፈጥሮ አከባቢን አስመልክቶ የሚፈጠሩ ችግሮችንና ሌሎች ብጥብጦችን ለመፍታት መጠቀም፡፡

ሐ) የሀገራት ደህንነታዊ መዋቅሮች ቅራኔን የማይፈጥሩ የመከላከያ መለያዎች አስከሚሆኑበት ደረጃ ድረስ ከሚሊተሪ ነፃ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡ እንዲሁም የሚሊተሪ ንብረቶችን ለሰላማዊ ጥቅም የኢኮሎጂ ጥገናዎችን ጨምሮ ማዋል፡፡

መ)ኑይክላር፣ ባይሎጂካል፣ መርዛማ እና ሌሎችም ጅምላ ጨፍጫፊ የሆኑየጦር መሳርያዎችን ማጥፋት፡፡

ሠ) ኦርቢታልና ውጫዊ የሆኑ የጠፈር ደጋፊ ነገሮችን ለተፈጥሮ አከባቢ ጥበቃና ለሰላም እንዲውል ማድረግ፡፡

ረ) ሰላም ሁለንተናዊ የሆነ በትክክለኛ ከራስ ጋር፣ ከሰው ጋር ከሌሎች ባህሎች ጋር፣ ከሌሎች የህይወት አካላት እና ሁላችንም ከምንገናኝበት ጠቅላላ የህይወት አካል ጋር ባለን ትክክለኛ ግንኙነት እንደሆነ መረዳት።

# የወደፊት አቅጣጫ

እስከአሁን በታሪክ ባልታየ ሁኔታ የጋራ እጣፈንታ መኖሩ አዲስ ጅማሬ እንድንፈልግ ምልክት እየሰጠን ይገኛል፡፡ ይህ ህዳሴ የዐርዝ ቻርተር መርሆዎች ቃል የሚገቡት ነው፡፡ ይህንን ቃል እንዲፈፀም የቻርተሩን አላማ እና እሴቶች ለመተግበርና ለማበረታት መስዋዕትነት መግባት አለብን፡፡ ይህ የአእምሮና ልባዊ የሆነ አመለካከት ለውጥ ይፈልጋል፡፡ አዲስ የሆነ አለማቀፋዊ መደጋገፍና ሃለፊነት ሊኖር ይገባል፡፡ ዘላቂ የሆነ የህይወት ራዕይን በአከካቢያችን፣በአገራችን፣ በክልላችንና በአለማችን ተጠበን መመስረትና መተግበር አለብን፡፡ የባህል ልዩነታችን ውድ የሆነ ቅርሳችን ነው እንዲሁም የተለያዩ ባህሎች በግላቸው ራዕዩን የሚተገብሩበት የራሳቸው የሆነ መንገድ ይፈልጋሉ፡፡

የዐርዝ ቻርተርን ለመመስረት ያበቃውን አለማቀፋዊ ውይይት ማጠናከርና ማስፋፋት አለብን፤ ተያይዞም ከተከታታዩ በትብብር ላይ የተመሰረተ እውነትንና ጥበብን ፍለጋ ብዙ የምንማረው አለን፡፡

ሕይወት ሁሌም በአስፈላጊ እሴቶች መሀከል የሚደረግ ውጥረትን ያካትታል፡፡ ይህ ማለት በጣም አስቸጋሪ የሆኑ ምርጫዎች ማለት ነው፡፡ ነገር ግን አንድነትና ልዩነትን፤ የሰውን ልጅ በነፃነት መመራትን ከጋራ ጥቅም መፈለግ፤ የአጭር ግዜ እቅድን ከረጅም ግዜ እቅድ የሚያቀናጅ መንገድ መፈለግ አለብን፡፡ሁሉም ሰው፣ ቤተሰብ፣ ድርጅት እና ማህበረሰብ የራሱ የሆነ የሚጫወተው ወሳኝ ሚና አለው፡፡ ጥበብ፣ ሳይንስ፣ ህይማኖት፣ የትምህርት ተቅዋማት፣ ሚዲያ፣ ቢዝነሶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና እና መንግስታት ሁሉም ፈጠራዊ የሆነ አመራር እንዲያሳዩ እድሉ ተሰጥቷቸዋል፡፡ እንዲሁም የመንግስት፣ ሲቪል ሶሳይቲ እና የቢዝነስ ትብብር ተክክለኛ የሆነ አመራር እንዲኖር ከማድረግ አንፃር ወሳኝ ነው፡፡ ዘላቂ የሆነ የአለም ማህበረሰብ ለመፍጠር፤ የአለም መንግስታት ለተባበሩት መንግስታት ያለባቸውን ግዴታና ሃለፊነት ማደስ አለባቸው፤ ተያይዞም በአለም አቀፋዊ ስምምነቶች ላይ መንግስታት የገቡትን ግዴታዎች መፈፀምና የተፈጥሮ አከባቢንና ልማትን አስመልክቶ በአለም አቀፍ በህግ በሚያስጠይቁ መንገዶች የየዐርዝ ቻርተርን መርሆዎች ትግበራ መደገፍ አለባቸው፡፡

የኛ ዘመን ለህይወት አዲስ ክብር እንዲሰጥ በማነሳሳት፤ ዘላቂነትን ለማምጣት ቁርጠኛ ተነሳሽነት ያለው፤ ፍትህና ሰላም እነዲኖር የሚደረግ ትግልን በማፋጠን፤ ደስተኛ የሆነ ህይወት እንዲኖር በማድረግ የሚታወስ ዘመን ይሁን፡፡